**ካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶች**

**ለተማሪዎች በውሰት ለሚሰጡ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች የተደረገ**

**የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ተጠቃሚ ስምምነት**

_______________ _______________ _________________
የተማሪው ስም የክፍል ደረጃ ቀን

______________ _________________
የተማሪው መታ. ቁጥር የወላጅ/አሳዳጊ ስም

የካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶች የኤሌክትሮኒክ መሳሪያና ከታች የተዘረዘሩት አጋዥ መሳሪያዎች የተሰጡኝ መሆን አረጋግጣለሁ፡ __________________________________________________

______________________________________________________(ከዚህ በኋላ ሁሉም በአንድ ላይ "የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ" እየተባሉ ይጠቀሳሉ)፡፡ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያው የተሰጠኝ ለትምህርት ዓላማ ብቻ መሆኑንና የኤሌክትሮኒክ መሳሪያው የካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶች ንብረት መሆኑንና የካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶች ንብረት ሆኖም እንደሚቀጥል፣ እኔም በካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶች በተማሪነት በመመዝገቤ በውሰት የተሰጠኝ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡ የካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶች የኤሌክትሮኒክ መሳሪያውን በማንኛውም ጊዜ ለመፈተሽ፣ በኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ላይ ተቀመጡ ማናቸውንም ፋይሎች ለመፈለግ መብቶ የተጠበቀ መሆኑንና በኤሌክትሮኒክ መሳሪያው ላይ የሚገኝ ማንኛውም መረጃ በግዛት የሕዝብ መረጃዎች መሰረት ይፋ ሊደረግ እንደሚችል፣ ነገር ግን በፌዴራልና በግዛት የተማሪ መዝገብ ሕጎችና መመሪያዎች መሰረት ይፋ እንዳይደረጉ ጥበቃ የተደረገላቸው መረጃዎች ግን በዚህ ውስጥ እንደማይካተቱ መረዳቴን አረጋግጣለሁ፡፡ በተጨማሪም፣ ከት/ቤቱ በሚቀርብልኝ ጥያቄ መሰረት የኤሌክትሮኒክ መሳሪያውን ለጥገና እና ፍተሻ መመለስ እንዳለብኝም እገነዘባለሁ፡፡

በተለይም ደግሞ፣ ለኤሌክትሮኒክ መሳሪያው መደረግ ያለበትን እንክብካቤ፣ ጥበቃና እድሳት በተመለከተ የሚከተሉትን መመሪያዎች ለመፈጸም ተስማምቻለሁ፡-

1. በማንኛውም ጊዜ የተመደበልኝ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ የት እንዳለ የማውቅ ሲሆን የኤሌክትሮኒክ መሳሪያው ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ውስጥ ካልተቀመጠ በስተቀር ምንጊዜም ከእኔ ጋር ይሆናል፡፡ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዬን በፍጹም ያለ ጠባቂ ትቼ አልሄድም፡፡ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዬ በጥሩ ሁኔታ እንዲሰራ ለማድረግና በውሃ፣ በብናኝ እና በአየር ሁኔታ መቀያየር፣ ማለትም ከፍተኛ ሙቀትና ቅዝቃዘን ጨምሮ፣ የሚደርስ ጉዳትን ለመከላከል ሲባል የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዬን ምቹ በሆነ ቦታ ማስቀመጥ እንደሚጠበቅብኝ እና የካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶችን ንብረት ለመጠበቅ ተገቢውን ግዴታ ለመወጣት እና የኤሌክትሮኒክ መሳሪያውን ከመጥፋት፣ ከመሰረቅ፣ ከመጎዳት ወይም ከመውደም መከላከል እንዳለብኝና የኤሌክትሮኒክ መሳሪያውንም በተዋስኩበት ተመሳሳይ ሁኔታ መመለስ እንዳለብኝ እገነዘባለሁ፡፡

2. የይለፍ ቃሎቼን በሚስጥርና ለግሌ እይዛለሁ፡፡ የይለፍ ቃሌ ሚስጥራዊ መሆኑ ካበቃ፣ ወዲያውኑ ለት/ቤቱ አስተዳደር አሳውቃለሁ፡፡

3. የተመደበልኝን በጭራሽ ለሌላ ሰው አላውስም፡፡

4. የፌዴራል የሕጻናት ኢንተርኔት ጥበቃ ሕግ (CIPA) የሚጠይቃቸውን ሁኔታዎች ለማሟላት ሲባል በኢንተርኔት ላይ የማደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ በካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶች ተቀባይነት ያለው አጠቃቀም ፖሊሲ መሰረት እንደሚሆንና ማጣሪያ እንደሚደረግበትም እገነዘባለሁ፡፡ በተመደበልኝ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ላይ የማካሂደው የኢንተርኔት ላይ እንቅስቃሴ ክትትል የሚደረግበት በት/ቤት ውስጥም ሆነ ከት/ቤት ውጭ መሆኑን እገነዘባለሁ፡፡

5. የተመደበልኝን የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ደህንነትና በትክክል መስራቱን ለማረጋገጥ ሲባል፣ የተመደበልኝ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ የደህንነት መከታተያ መሳሪያ የተጫነበት መሆኑንና ይህም ሁሉንም የመሳሪያውን ተግባራት እንደሚመዘግብ፣ የካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶችም የመሳሪያውን እንቅስቃሴ የመከታተል መብቱ የተጠበቀ መሆኑን እገነዘባለሁ፡፡

6. ምግብና መጠጥ የተመደበልኝን የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ሊጎዱ ስለሚችሉ ከመሳሪያው እንዲርቁ አደርጋለሁ፡፡

7. በኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ላይ ምልክት ማድረግ፣ ስዕል መሳል፣ መጻፍ ወይም ስቲከር መለጠፍ አልችልም፡፡

8. የተመደበልኝን የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ የትኛውም ክፍል ላይ መነቃቀል፣ ወይም ማንኛውም ጥገና፣ ማሻሻያ፣ ማዘመኛ ወይም ለውጦችን ላይ አላደርግም (ይህን ካደረግሁ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያው ዋስትና ዋጋ አይኖረውም)፡፡ በተጨማሪም፣ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያውን ፎርማት አላደርግም፣ የደህንነት ቅንብሮቹን አልነካካም፣ ወይም ኦፐሬቲንግ ሲስተሙን አልቀይርም ወይም ማንኛውንም ሶፍትዌር አልጭንም፡፡ በተጨማሪም፣ በሲፒኤስ የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አገልግሎቶች መምሪያና በት/ቤት አስተዳዳሪው ካልተፈቀደለኝ በስተቀር የኤሌክትሮኒክ መሳሪያውን ከኢንተርኔት ሶፍትዌር፣ ሙዚቃ ወይም ሌሎች ፕሮግራሞችን ለማውረድ አልጠቀምም፡፡

9. መጫር፣ መሰንጠቅ ወይም መበሳትን ጨምሮ ማንኛውም ጉዳት ወይም ውድመት ከደረሰ፣ ጉዳቱን ለ CRLS የቴክኖሎጂ ማዕከል የማሳውቅ ሲሆን የኤሌክትሮኒክ መሳሪያው ጥገና የሚያስፈልገው ከሆነም ወዲያውኑ ለት/ቤቱ አስተዳደር እመልሳለሁ፡፡

10. የኤሌክትሮኒክ መሳሪያው ቢሰረቅ፣ ወይም ቢጠፋ፣ ለትምህርት ማህበረሰብ ጽ/ቤቱ በአፋጣኝ አሳውቃለሁ፡፡

11. የካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶች ተቀባይነት ያለው አጠቃቀም ፖሊሲ፣ የሶፍትዌር ስነ-ምግባር ደንብ እና የመብቶችና ኃላፊነቶች መምሪያ መጽሐፍ እንደዚሁም ማንኛውም ት/ቤት ነክ ደንቦችን አከብራለሁ፡፡ ተቀባይነት ያለው አጠቃቀም ፖሊሲ፣ የሶፍትዌር ስነ-ምግባር ደንብ እና የመብቶችና ኃላፊነቶች መምሪያ መጽሐፍ እና/ወይም የት/ቤት ነክ ደንቦችን የሚጻረር ማንኛውም ተገቢነት የሌለው ባህርይ የዲስፕሊን እርምጃ ሊያስወስድብኝ እንደሚችል፣ በዚህም ውስጥ የልዩ መብቶች እገዳ ወይም ስረዛ፣ ከት/ቤት መታገድ ወይም መባረር እና/ወይም በወንጀል መከሰስ እንደሚካተት እገነዘባለሁ፡፡

12. በሕጋዊ መንገድ ያልተገኘ ሚድያ ወይም ሶፍትዌርን ማውረድን የሚከለክሉ አግባብነት ያላቸውን የቅጂ መብትና የሶፍትዌር ፈቃድ ስምምነቶችን በሙሉ አከብራለሁ፡፡

13. የተመደበልኝን የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ወይም ሌላ ማንኛውንም የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ በመጠቀም ሰዎችን ለመጉዳት በማሰብ በማንኛውም የትንኮሳ፣ የማንጓጠጥ ወይም የዛቻ ተግባራት (ማንጓጠጥ እና/ወይም በኢንተርኔት በኩል ማንጓጠጥን ጨምሮ) ውስጥ አልሳተፍም፡፡

14. የተመደበልኝን የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ በተጠየቅኩ ጊዜ ለት/ቤቱ አስተዳዳሪ (ወይም ለተወካዩ) እመልሳለሁ፡፡ ትምህርት ካቋረጥኩ፣ ከተባረርኩ ወይም በማንናውም ምክንያት በት/ቤቱ ውስጥ ያለኝን ምዝገባ ካቋረጥኩ፣ በት/ቤቱ በሚኖረኝ የመጨረሻው የምዝገባ ቀን የተመደበልኝን የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ለት/ቤቱ አስተዳዳሪ (ወይም ለተወካዩ) እመልሳለሁ፡፡

15. የኤሌክትሮኒክ መሳሪያው ወቅታዊ ዋጋ _______ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያው ሆን ተብሎም ሆነ በቸልተኝነት ምክንያት ቢጠፋ፣ ቢሰረቅ፣ ቢጎዳ ወይም ቢበላሽ፣ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያውን ለመተካት ከሚወጣው ወጪ ጋር በተያያዘ ለካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶች ወጪውን ተመላሽ ለማድረግ ኃላፊነት እንዳለብኝና የካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶች ለጠፋው፣ ለተሰረቀው፣ ለተጎዳው ወይም ለተበላሸው የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ወጪ ለመሸፈን የእኔን ገንዘብ እንዲሰበስብ እገዛ ለመስጠት ተስማምቻለሁ፡፡ በተጨማሪም፣ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያውን ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆንኩ እና/ወይም ካልቻልኩ፣ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያውን ለመተካት ከሚወጣው ወጪ ጋር

በተያያዘ ለካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶች ወጪውን ተመላሽ የማድረግ ኃላፊነት እንዳለብኝ የተገነዘብኩና የተስማማሁ ሲሆን ካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶችም የኤሌክትሮኒክ መሳሪያውን ለመተካት ከሚወጣው ወጪ ጋር በተያያዘ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያውን ለማስመለስ እና/ወይም ወጪውን ለመሸፈን አግባብነት ያላቸውን ሌሎች አማራጮች እንደሚጠቀም ተስማምቻለሁ፡፡

16. ካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶች የኤሌክትሮኒክ መሳሪያውን እና የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተመለከተ በግልጽም ሆነ በታሳቢነት ምንም ዓይነት ዋስትና እንደማይሰጥ እገነዘባለሁ፡፡ ካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶች ለማንኛውም ጉዳት፣ የዳታ መጥፋት፣ የአገልግሎት መቋረጥ፣ መዘግየት፣ መቅረት ወይም በትክክል አለመቅረብ ምክንያት ምንም ዓይነት ኃላፊነት እንደማይኖርበት እገነዘባለሁ፡፡ ካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶች በየትኛውም ኔትወርክ ወይም ኢንተርኔት ላይ ለተከማቸ ወይም ለተላለፈ መረጃ ትክክለኛነት ወይም ጥራት ኃላፊ እንደማይሆንና እንዲህ ዓይነት መረጃ የምጠቀመው በራሴ ኃላፊነት መሆኑንም እገነዘባለሁ፡፡ ካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶች በየትኛውም ኔትወርክ ወይም ኢንተርኔት አጠቃቀም ምክንያት ለሚከሰት የፋይናንስ ግዴታ ኃላፊ እንደማይሆንና ከተማሪው ወይም ወደተማሪው የዳታ ማከማቻ መሳሪያ ሊተላለፍ ለሚችል ማንኛውም የኮምፒዩተር ወይም ኤሌክትሮኒክ ቫይረስ ወይም ጎጂ ፕሮግራም ኃላፊነት እንደሌለበት እገነዘባለሁ፡፡

ተማሪው እና ወላጆቹ/አሳዳጊዎቹ ከዚህ በታች ፊርማቸውን በማስፈር በዚህ ለተማሪዎች በውሰት ለሚሰጡ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች የተደረገ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ተጠቃሚ ስምምነት ውስጥ በተቀመጡት ሁኔታዎችና ካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶች የኮምፒዩተር እና ኔትወርክ ስርዓቶች አጠቃቀም በወጣው የካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶች ተቀባይነት ያለው አጠቃቀም ፖሊሲ፣ በካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶች የሶፍትዌር ስነ-ምግባር ደንብ እና በካምብሪጅ የሕዝብ ት/ቤቶች የመብቶችና ኃላፊነቶች መምሪያ መጽሐፍ እና በየትኛውም የት/ቤት ነክ ደንቦች ለመገዛት ተስማምተዋል፡፡ ተማሪው እና ወላጆቹ/አሳዳጊዎቹ እያንዳንዳቸው ይህን ለተማሪዎች በውሰት ለሚሰጡ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች የተደረገ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ተጠቃሚ ስምምነት ማንበባቸውንና ሁኔታዎቹንም መረዳታቸውንና በራሳቸው ፈቃድና ያለውን ዋጋ ሙሉ በሙሉ በመገንዘብ ፊርማቸውን ማስፈራቸውንም ያረጋግጣሉ፡፡

| | |
|---|---|
| ____________________ | ________________________ |
| የተማሪው ስም | የተማሪው ፊርማ |
| _______________________ | _________________________ |
| የወላጅ/አሳዳጊ ስም | የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ |
| ___________________ | __________________ |
| ቀን | CPSD ሐብት መለያ ቁጥር |

**የኤሌክትሮኒክ መሳሪያን ወደ ቤት መውሰድ - ስምምነትን ማቋረጫ**

ከላይ የተዘረዘሩትን ኃላፊነቶች በሙሉ አንብቤ የተረዳሁ ሲሆን ልጄ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ወደቤት እንዲወስድ <u>አልፈልግም</u> ፡፡ በተጨማሪም፣ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያው በትምህርት ሰዓት አሳይመንቶችን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልግ ቢሆን የኤሌክትሮኒክ መሳሪያውን ማግኘት እንደሚችልና የኤሌክትሮኒክ መሳሪያው ከትምህርት ሰዓት ውጭ አሳይመንቶችን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልግ ከሆነና አሳይመንቱም በቀላሉ በሃርድ ኮፒ ሊባዛ የሚችል ከሆነ፣ ት/ቤቱ ልጄ ወደቤት

የሚወስደው ሃርድ ኮፒ ማቴሪያል እንደሚያቀርብ እና/ወይም በራሱ ውሳኔ ከመደበኛ የመማሪያ ሰዓት ውጭ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያውን በካምፓስ ሊያቀርብ እንደሚችልም እገነዘባለሁ፡፡

____________________ ____________________
የተማሪው ስም የተማሪው ፊርማ

____________________ ____________________
የወላጅ/አሳዳጊ ስም የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ

____________________
ቀን